ከስህተት መማር

ራስህን ለመገምገም የሚረዳህ ይህ መልመጃ (1) ስህተት ስትሠራ ምን ማድረግ እንደሚቀናህ እና (2) ወደፊት ስህተት ብትሠራ ሁኔታውን በተሻለ መንገድ መያዝ የምትችለው እንዴት እንደሆነ ለማወቅ ይረዳሃል።

ምን ይመስልሃል?

1 አንዳንድ ወጣቶች ስህተታቸውን አምነው መቀበል የሚከብዳቸው ለምንድን ነው?

.....

.....

.....

.....

.....

.....

.....



ምሳሌ፦ “ስህተቴን ለራሴ መቀበል አይከብደኝም፤ ስህተት መሥራቴን በሌሎች ፊት መቀበል ግን በጣም ይከብደኛል። ሰዎች ስለ እኔ መጥፎ አመለካከት እንዲኖራቸው አልፈልግም።”—ሜሊንዳ

2 ሁልጊዜ ስህተትህን ለመሸፋፈን የምትሞክር ከሆነ ሰዎች ስለ አንተ ምን ዓይነት አመለካከት ይኖራቸዋል?

.....

.....

.....

.....

.....

.....

.....

ምሳሌ፦ “ስህተት ሠርተህ ለመሸፋፈን የምትሞክር ከሆነ ሰዎች ስለ አንተ ጥሩ አመለካከት አይኖራቸውም። ሰዎች ስህተትህን ማለፍ ላይከብዳቸው ይችላል፤ ስህተትህን በመደበቅ እነሱን ለማታለል መሞከርህ ግን ያበሳጫቸዋል።”—ክርስቲን

3 ስህተትህን ምንም ሳታንገራግር አምነህ የምትቀበል ከሆነ ሰዎች ስለ አንተ ምን አመለካከት ይኖራቸዋል?

.....

.....

.....

.....

.....

.....

.....

ምሳሌ፦ “ስህተቴን አምኜ የተቀበልኩባቸው ጊዜያት ትዝ ይሉኛል፤ በዚህ ጊዜ ሰዎች ለእኔ ያላቸው ግምት አልቀነሰም፤ እንዲያውም ለእኔ ያላቸው አክብሮት ጨምሯል።”—ሪቻርድ

www.jw.org/am © 2014 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

አንተ ብትሆን ምን ታደርጋለህ?



የአባትህን ብስክሌት ተውሰህ ስትነዳ ተበላሽብህ።

- ☐ አባትህ እንደማያስተውለው በማሰብ ዝም ትላለህ?
- ☐ ስለተፈጠረው ነገር ለአባትህ በግልጽ ትነግረዋለህ?
- ☐ ጉዳዩን ለአባትህ ብትነግረውም ጥፋቱን በሌላ ሰው ላይ ታላክካለህ?



ኳስ ስትጫወት የጎረቤትህን መስኮት ሰበርክ እንበል።

- ☐ ትሮጣለህ?
- ☐ ለጎረቤትህ አውነቱን በመናገር ላደረስከው ጉዳት ካሳ መክፈል እንደምትፈልግ ትገልጻለህ?
- ☐ ጥፋቱን በሌላ ሰው ላይ ታላክካለህ?



አንድን ትምህርት ባለማጥናትህ ፈተናውን ወደቅክ።

- ☐ ፈተናው ቸግር አንዳለው ትገልጻለህ?
- ☐ ፈተናውን የወደቅኸው በራስህ ጥፋት እንደሆነ አምነህ ትቀበላለህ?
- ☐ አስተማሪው እንደሚጠላህ ትናገራለህ?

እስቲ አሁን ደግሞ ራስህን (1) በአባትህ፣ (2) በጎረቤትህ እንዲሁም (3) በአስተማሪህ ቦታ አስቀምጠህ ከላይ ያሉትን ሁኔታዎች ለማሰብ ሞክር።

ስህተትህን አምነህ የምትቀበል ከሆነ አባትህ፣ ጎረቤትህ እንዲሁም አስተማሪህ ስለ አንተ ምን ዓይነት አመለካከት ይኖራቸዋል?

.....

.....

.....

.....

.....

ስህተቱን በሌላ ሰው ላይ ለማላከክ ወይም ለመሸፋፈን ብትሞክር ስለ አንተ ምን ይሰማቸዋል?

.....

.....

.....

.....

.....

www.jw.org/am © 2014 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

ባለፈው ዓመት የሠራኸውን አንድ ስህተት ለማስታወስ ሞክር።

ስህተቱ ምን ነበር?

.....

.....

.....

ስህተቱን ከሠራህ በኋላ ምን አደረግህ?

☐ ስህተቱን ለመደበቅ ሞክርኩ።

☐ ጥፋቴን በሌላ ሰው ላይ አላከክሁ።

☐ ጥፋቴን አምኜ ተቀበልኩ።

በወቅቱ ጥፋትህን *ሳታምን ቀርተህ* ከነበረ፣ በኋላ ላይ ምን ተሰማህ?

☐ ደስ አለኝ፤ ሳልያዝ አመለጥኩ!

☐ ጥፋተኝነት ተሰማኝ፤ ስህተቴን መናገር ነበረብኝ።

ሁኔታውን በተሻለ መንገድ ለመያዝ ምን ማድረግ ችችል ነበር?

.....

.....

.....

.....

.....

ከስህተትህ ምን ተማርክ?

.....

.....

.....

.....

.....

ስህተት ስትሠራ ጉዳዩን በምትይዝበት መንገድ ረገድ በቀጣዩ ዓመት ውስጥ ምን ማሻሻያ ለማድረግ ወስነሃል?

.....

.....

.....

.....

.....



ተጨማሪ ሐሳብ ለማግኘት፦

ስለዚህ ጉዳይ ምርምር ማድረግ ከፈለግህ ኃጢአቱን ስለተናዘዘው ስለ ዳዊትና ከእሱ በተቃራኒ ለስህተቱ ሰበብ ስላቀረበው ስለ ሳኦል የሚገልጹ ታሪኮችን 2 ሳሙኤል 12:1-13 እና 1 ሳሙኤል 15:10-26 ላይ ማንበብ ትችላለህ።

ከዚያም የሚከተለውን ነጥብ አስብ፦ ዳዊትም ሆነ ሳኦል ጥፋታቸውን ወዲያውኑ አላመኑም፤ ይሁንና ሁለቱም *ከጊዜ በኋላ* ስህተታቸውን አምነው መቀበላቸው አልቀረም። ታዲያ ይሖዋ አምላክ ዳዊትን ይቅር ያለው፣ ሳኦልን ግን ይቅርታ ያላደረገለት ለምንድን ነው?

www.jw.org/am © 2014 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania